| ዘአክርስቶዶሎስ ፡ ም ፡ ፪፲፪ ። | ዘአክርስቶዶሎስ ፡ ም ፡ ፪፲፪ ። |
|---|---|
| ፲፫ ፡ ንሕነሰ ፡ ኦርቶዶክሳውያን ፡ ኢንብል ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ በከመ ፡ ሐለዩ ፡ አብዳን ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ልብ ፡ ወልቡና ፡ እንዘ ፡ ይሔልዩ ፡ ከመ ፡ ጠቢባን ፡ እሙንቱ ፡ ወለነሰ ፡ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ሃይማኖትነ ፡ እ ፡ እግዚእ ፡ በአብ ናከ ፡ ወርኅሩኅ ፡ ልብ ፡ ወፅሩየ ፡ ነፍስ ፡ በተአኅዎ፡ መንፈሳዊ ፡ ወበሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወውእቱ ፡ አምሳሊሆሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ ዘሠረቀ ፡ ብርሃኑ ፡ በመልእክት ፡ ሐዋርያዊት ፡ ማእከለ ፡ ፪ቱ ፡ መናብርት ፡ ክቡራን ፡ ዘውእቶሙ ፡ መንበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ክቡር ፡ ወመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ሰባኪ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ጽድቅት ፡ ኦርቶዶክሳዊት ። | ፲፫ ፡ እኛ ፡ ኦርቶዶክሳውያን ፡ ዐዋቂዎች ፡ ነን ፡ ሲሉ ፡ ልብ ፡ ዕውቀት ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ለጌታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ አንልም ፤ የእኛስ ፡ ሃይ ማኖታችን ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ በአባትነትህ ፡ ገዥ ፡ ልበ ርኅሩኅ ፡ የምትሆን ፤ በቀናች ፡ ሃይማኖትና ፡ በመን ፈሳዊ ፡ ተዘምዶ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የምትሆን ፡ ሐዋርያትን ፡ የምትመስል ፤ ከሐዋርያት ፡ በተገኘ ሹመት ፡ ትምህርትህ ፤ ክቡራን ፡ በሚሆኑ ፡ በሁ ለቱ ፡ መናብርት ፡ መካከል ፡ የታወቀ ፤ እነዚህም ፡ የከበረች ፡ የጴጥሮስ ፡ መንበርና ፡ (አንጾኪያ)፡ኦርቶ ዶክሳዊት ፡ ሃይማኖታችንን ፡ የሚያስተምር ፡ የማ ርቆስ ፡ መንበር ፡ (እስክንድርያ) ፡ ናቸው ። |
| ፲፬ ፤ ወመሠረተ ፡ ምሥጢር ፡ ወመራሒተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወመርሶ ፡ መድኃኒት ፡ እንተ ፡ ትወስድ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ወሥነ ፡ ተዘምዶ ፤ ዘያስተጋብእነ ፡ ኅቡረ ፡ ወይትረከብ ፡ ውስቴትነ ፡ ወበእንተ ፡ ምሥጢር ፡ ዐቢይ ፡ ዘአምልኮ ፡ ፍጽ ምት ፡ ወሐመር ፡ ጽንዕት ፡ እንተ ፡ ታድኅን ፡ እሞ ገደ ፡ ማዕበላት ፡ ወታበጽሕ ፡ ኀበ ፡ መርሶ ፡ ፍሥሓ፡ ወኃሤት ፡ ወተድላ ፡ ወዕንቍ ፡ ክብርት ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡ ሤጥ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓተ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘባቲ ፡ ረከብነ ፡ ኵልነ ፡ አእምሮቶ ፡ ለአምላክነ ፡ ከሀሊ ፡ ዘኢይትመዋእ ፡ ወባቲ ፡ ሞእነ ፡ ኵሎ ፡ ወባቲ ፡ ንትዌከል ፡ ወባቲ ፡ ንትአኀዝ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ሕይወት ። | ፲፬ ፤ የምሥጢር ፡ ባለቤት ፡ ናት ፤ ወደ ፡ ቀናች ፡ ሃይማ ኖት ፡ የምትመራ ፡ ናት ፤ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ሕይወ ትና ፡ አንድ ፡ ወደ ፡ አደረገን ፡ ፍጹም ፡ አምልኮ ታችንን ፡ ስለምንገልጥበት ፡ ደገኛ ፡ ምሥጢር ፡ በእኛ ፡ ወደሚገኝ ፡ ወደ ፡ በጐ ፡ ተዘምዶ ፡ የምትወ ስድ ፡ የድኅነት ፡ ወደብ ፡ ናት ፤ ከሚነዋዋ ፡ ማዕበል ሞገድ ፡ የምታድን ፤ ፍጹም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ወደ አለበት ፡ ወደብ ፡ የምታደርስ ፤ የጸናች ፡ መርከብ፡ ናት ፤ የማይመረመር ፤ ሁሉን ፡ የሚችል ፡ ፈጣሪያ ችንን ፡ ማወቅን ፡ ሁላችን ፡ ያገኘንባት ፤ ሁሉንም፡ ድል ፡ የነሣንባት ፡ ተስፋ ፡ የምናደርጋት ፤ እስከ፡ ዘመናችን ፡ ፍጻሜ ፡ በእርሷ ፡ ጸንተን ፡ የምንኖርባት ሃይማኖታችን ፡ በእርሷ ፡ ጸንታ ፡ የምትኖር ፡ ስለ ሆነ ፡ ዋጋ ፡ የማይገኝላት ፡ የከበረች ፡ ዕንቍ ፡ ናት ። |
| ፲፭ ፤ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወእምነት ፡ ጽንዕት ፡ ዘአልባቲ ፡ ፍርኀት ፡ ወድንጋፄ ፡ በዝ ዓለም ፡ ኀላፊ ፡ ወበዘይመጽእ ፡ ዓለም ፡ ወባቲ ፡ ንሴፎ ፡ ሕይወተ ፡ በዓለም ፡ ደኃሪት ፡ እንተ ፡ ትነ ብር ፡ ለዓለም ፡ በአስተርእዮቱ ፡ ደኃሪት ፡ ለእግዚ እነ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ፡ በግርማ ፡ መፍርህ ፡ ዘሀለዎ ፡ ያስተርኢ ፡ በስብሐተ ፡ መለኮቱ ፡ አም ላካዊ ፡ ምስለ ፡ መላእክቲሁ ፡ ቅዱሳን ፡ ኄራን ፡ ወልጹቃን ፡ ከመ ፡ ይኰንኖን ፡ ሕያዋነ ፡ ወሙታነ ፡ | ፲፭ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፤ በማያልፈውም ፡ ዓለም ፡ ፍርሃት፡ ድንጋጤ ፡ የሌለባት ፤ የቀናች ፡ ፍጽምት ፡ ሃይማ ኖት ፡ ይህች ፡ ናት ፤ ማለፍ ፡ በሌለባት ፡ በኋላ ኛዪቱ ፡ ዓለም ፤ በኃጥአን ፡ ሊፈርድባቸው ፤ ለጻድ ቃን ፡ ሊፈርድላቸው ፡ በቅዳሴ ፡ አንድ ፡ የሚሆኑ ፡ ክቡራን ፡ ኄራን ፡ መላእክትን ፤ አስከትሎ ፡ በአም ላካዊ ፡ ጌትነቱ ፡ ክብር ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚያስፈራ ፡ ግርማ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ በእርሷ ፡ መዳንን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። |
| ፲፮ ፤ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ርስት ፡ ዘየዐቢ ፡ ወይፈደፍድ ፡ ወብዕል ፡ ዐቢይ ፡ ዘወረስናሁ ፡ እምአበው ፡ ቅዱ ሳን ፡ ወክቡራን ፡ ወተምህርናሁ ፡ እምአጋእዝቲነ ፡ ሐዋርያት ፡ ሰባክያን ፡ አብራህያን ፡ ዓለም ፡ እለ ፡ ተፈነዉ ፡ ኀቤነ ፡ ወአብርሁ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ በትምህርታቲሆሙ ፡ ብርህት ፡ ወጽድቅት ። | ፲፮ ፤ ፍጹም ፡ የማያልፍ ፡ ርስት ፤ ንጹሓን ፡ ከሚሆኑ ፡ አባቶች ፡ የወረስነው ፡ ፍጹም ፡ ክብር ፤ በኀላች ፡ በተረዳች ፡ ትምህርታቸው ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ፡ ከአደረጉ ፤ ወደ ፡ እኛ ፡ ከተላኩ ፤ ወንጌልን ፡ ከሚ ያስተምሩ ፡ ከጌቶቻችን ፡ ከሐዋርያት ፡ የተማር ነው ፡ ትምህርት ፡ ይህ ፡ ነው ። |

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፫ ። ም ፡ ፻፲፱ ።

፲፱ ፤ ንሕነሰ ፡ ክርስቶሳውያን ፡ ናርሕቅ ፡ እምኔነ ፡ እሎንተ ፡ እምንታተ ፡ ርኩሳተ ፡ ወንትዌከፍ ፡ ተዋሕዶተ ፡ ዘኢይትፈለጥ ፡ ወዘኢይትከፈል ፡ ወዘኢይቱሳሕ ፡ ወንጸመድ ፡ በርትዕ ፡ ለሃይማኖት ፡ ጽድቅት ፡ እንተ ፡ ዘአበዊነ ፡ ርቱዐነ ፡ ሃይማኖት ፤ ንሰግድ ፡ ወንትቀነይ ፡ ለክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ዘአስተጋብአነ ፡ ላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወቅድስት ፤ ወንገኒ ፡ ለመለኮተ ፡ አምላክነ ፡ ዘኢይትከፈል ፡ ወዘኢይትዌለጥ ፡ ወዓዲ ፡ ንትላጸቅ ፡ በጽድቀ ፡ ወንጌሉ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ በኪዳን ፡ ሐዲስ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ እምንትነ ፡ ላዕለ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ በፍሥሓ ፡ ወበሐሤት ።

፳ ፤ ወንስእል ፡ ለነገሥትነ ፡ ምእመናን ፡ ከመ ፡ የሀቦሙ ፡ ሥልጣነ ፡ ወኀይለ ፡ ወመዊአ ፡ ወለኵሉ ፡ ዓለም ፡ ሣህለ ፡ ወምሕረተ ፡ ወለአብያተ ፡ ክርስቲያናትኒ ፡ ወለምኔታት ፡ ዛኅነ ፡ ወመርሰ ፡ ሰላመ ፡ ወህድአተ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

<u>ምዕራፍ ፡ ፻፲፬ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።</u>

፩ ፤ እመልእክተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአብ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ ፡ ወሀገረ ፡ ምሥራቅ ፡ ወእለ ፡ ምስሌሃ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ አክርስቶዶሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ፡ ወግብጽ ፡ ወኖባ ፡ ወኢትዮጵያ ፡ ወምዕራብ ፤ ናሁ ፡ ነአምን ፡ ወንትአመን ፡ በልብ ፡ ወበአእምሮ ፡ ወልባዌ ፡ እምኵሉ ፡ ነፍስ ፡ እምነተ ፡ ጽድቅተ ፡ ዘይደሉ ፡ ላዕለ ፡ ሃይማኖት ፡ ክብርት ፡ ዘትትሌዐል ፡ እምኵሉ ፡ ክብር ፡ በአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፪ ፤ ሥላሴ ፡ በተዋሕዶ ፡ ልዑላን ፡ ወቀዳማውያን ፡ ዕሩያን ፡ ህላዌ ፡ ወዕሩያን ፡ መለኮት ፡ ወኀይል ፡ በአሐቲ ፡ ሥልጣን ፡ ወበ፩ዱ ፡ ፈቃድ ፡ ወበአሐቲ ፡ ሥምረት ፡ ወበፈጢረ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ፡ ወ፫ቱ ፡ ገጻት ፡ ቅዱሳን ፡ ወፍጹማን ፡ ወአልቦ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ሕጸት ፡ ወኢፍድፋዴ ፡ አላ ፡ ፍጹማን ፡ ወዕሩያን ፡ እሙንቱ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ እምአካላት ፡ ህልዋን ፡ በበአካላቲሆሙ ፡ ኅቡራን ፡ ህላዌ ፡ ወመለኮት ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ወላዲ ፡ ወዘተወልደ ፡ ወዘሠረጸ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፻፲፫ ። ም ፡ ፻፲፱ ።

፲፱ ፤ ኦርቶዶክሳውያን ፡ እኛ ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ የረከሱ ፡ እምነቶችን ፡ ከእኛ ፡ እናርቃለን ፤ የማይለይ ፤ የማይከፈል ፤ የማይቀላቀል ፤ ተዋሕዶን ፡ እናምናለን ፤ ሃይማኖታቸው ፡ የቀናች ፡ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ ላመኑባት ፤ ለተረዳች ፡ ሃይማኖት ፡ በቅን ፡ እናገለግላለን ፤ በዚች ፡ በተመረጠች ፤ በከበረች ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ላደረገን ፡ ለፈጣሪያችን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንገዛለን ፤ እንሰግዳለን ፤ የማይከፈል ፤ የማይለወጥ ፡ የሆነ ፡ የፈጣሪያችንን ፡ ባሕርይ ፡ እናምናለን ፡ ዳግመኛ ፤ በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ሆነን ፡ ለዘላለሙ ፡ በወንጌል ፡ ጸንተን ፡ እንኖራለን ፤ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ብለን ፡ የምናምነው ፡ እምነት ፡ ይህ ፡ ነው ።

፳ ፤ ለታመኑ ፡ ነገሥታት ፤ ሥልጣንን ፤ ኃይልን ፤ ድል ፡ መንሣትን ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፤ ለዓለሙም ፡ ሁሉ ፡ ይቅርታን ፤ ቸርነትን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፤ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፤ ለገዳማትም ፤ ጸጥታን ፤ ርካታን ፤ ፍቅርን ፤ አንድነትን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እንለምን ፡ አሜን ።

<u>ምዕራፍ ፡ ፻፲፬ ፡ ክፍል ፡ ፪ ።</u>

፩ ፤ የአንጾኪያ ፤ የሶርያ ፤ የባቢሎን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ የእስክንድርያ ፤ የግብጽ ፡ የኖባ ፤ የኢትዮጵያ ፤ የሰናር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ ሚሆን ፡ ወደ ፡ አባ ፡ አክርስቶዶሎስ ፡ ከላከው ፡ መልእክቱ ፤ በልብ ፤ በዕውቀት ፤ ከፍጥረትም ፡ ሁሉ ፡ በተለየ ፡ ማስተዋል ፤ ከክብር ፡ ሁሉ ፡ ለምትበልጥ ፡ ለከበረች ፡ ሃይማኖት ፡ እንደሚገባ ፡ የተረዳች ፡ እምነትን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እናምናለን ፤ እንታመናለን ።

፪ ፤ ሥላሴ ፡ በአንድነት ፡ የማይመረመሩ ፡ ቀዳማውያን ፡ ናቸው ፤ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ በመለኮት ፡ በኀይል ፤ በአንዲት ፡ ሥልጣን ፤ በአንድ ፡ ፈቃድ ፤ በአንዲት ፡ ውድ ፤ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ በመፍጠር ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ ሦስቱ ፡ አካላት ፤ ሦስቱ ፡ ገጻት ፡ ፍጹማን ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸው ፡ በእነሱ ፡ ማነስ ፡ መብዛት ፡ የለባቸውም ፤ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ የተካከሉ ፡ ፍጹማን ፡ ናቸው ፤ እንጂ ፤ ከአካላት ፡ እያንዳንዱ ፡ ሁሉም ፡ በየአካላቸው ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፤ ባለመለየት ፡ በባሕርይ ፤ በመለኮት ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ እነዚህም ፤ የወለደ ፡ አብ ፤ የተወለደ ፡ ወልድ ፤ የሠረጸ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ናቸው ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፩፲፬ ።

፲፫ ፤ ወተሰምየ ፡ ስሙ ፡ ዐማኑኤልሃ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡
አምላክነ ፡ ምስሌነ ፤ ወውእቱ ፡ ፩ዱ ፡ ገጽ ፡ ወ፩ዱ ፡
ህላዌ ፡ ወ፩ዱ ፡ አካል ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘተ
ሠገወ ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወኢትድምርት ፡ ወኢቱ
ሳሔ ፡ ዘእንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ማእከለ ፡ ፪ቱ ፡ ህላ
ዌያት ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘኢይት
ክፈል ፡ ዘውእቶሙ ፡ መለኮት ፡ ወትስብእት ፡ ወተ
ዋሕደ ፡ ረቂቅ ፡ በሥጋ ፡ ገዚፍ ፡ ምስለ ፡ ህላዌ ፡
ሥጋ ፡ እንተ ፡ አልቦቱ ፡ ነውር ፡ ዘእንበለ ፡ ፍል
ጠት ፡ ወኢውላጤ ፡ ወኢዘከረ ፡ መጽሐፍ ፡ ፪ተ ፡
እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘኢይትነገር ፡ ወዘኢይትዌ
ሰን ፡ ወለብሰ ፡ ሥጋ ፡ መዋቴ ፡ እሙነ ፡ ወኢኮነ ፡
ምትሀተ ፡ ወኢነሥአ ፡ ክፍለ ፡ እምኔሁ ፡ ወባሕቱ ፡
ፈጸመ ፡ ኵሎ ፡ ዘዚአነ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕ
ቲታ ፡ ወኮነ ፡ ዕሩየ ፡ ምስሌነ ።

፲፬ ፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተወክፈ ፡ ኵሎ ፡ ዘዚአነ ፡ ርኀበ ፡
ወጸምዓ ፡ ኖመ ፡ ወደከመ ፡ እምሐዊረ ፡ ፍኖት ።
ተነከነ፡ ተሰቅለ ፡ ወሐመ ፡ ወተቀንወ ፡ ወበጽሐ ፡
ለሞት ፡ በፈቃዱ ፡ በከመ ፡ ነገራ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻ
ሕፍት ፡ ምሥጢር ፡ ዐቢይ ፡ ወግሩም ፡ ውእቱ ፡
ትስብእቱ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ወይሁበከ ፡ ተፈልጦተ ፡
ወተከፍሎተ ፡ ወተዋሕዶተ ።

፲፭ ፤ ወእመሰ ፡ ተብህለ ፡ ኮነ ፡ መድኃኒትነ ፡ በሰብእ ፡
ዝንቱ ፡ ዕልወት ፡ ወክሒድ ፡ ውእቱ ፡ ዳእሙ ፡ መድ
ኃኒትነሰ ፡ ኮነ ፡ በአምላክ ፡ ዐቢይ ፡ መንክር ፡ ወመ
ድምም ፡ ውእቱ ፡ ከዊነ ፡ አምላክ ፡ ሰብአ ፡ ፍጹመ ፡
ወዝንቱሰ ፡ ኮነ ፡ በመንክር ፡ ግብር ፡ ዘይትዐዶ ፡
እምልበ ፡ ዕጓለ ፡ ሕመሕያው ፡ ከዋኔ ፡ ሥርዓቱ ፡
ለአምላክ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክል ፡ መኑሂ ፡ ፍካሬሁ ፡
ወኢዘከመ ፡ እፎ ፡ ውእቱ ፡ ዕጹብ ፡ ወመንክር ፡
ውእቱ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌሁ ፡ ለአምላክነ ፡ ቃል ።
ወኢሳይያስኒ ፡ ሰመዮ ፡ መንክረ ፡ ወመድምመ ፡
በግብር ፡ ዘኢይትነገር ፡ ወዘኢይትረከብ ፡ ወለሊሁ ፡
ይትሌዓል ፡ እምልቡና ፡ ሰብእ ፡ ወርሑቅ ፡ ውእቱ ፡
እምኵሉ ፡ ምትሀት ፡ ወተዐቅፎ ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፮ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፩፲፬ ።

፲፫ ፡ ስሙም ፡ ዐማኑኤል ፡ ተባለ ፤ ትርጓሜውም ፡ አም
ላካችን ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡
ነው ፤ የማይከፈል ፡ ተዋሕዶ ፡ ከእነሱ ፡ በተደረገ
ባቸው ፡ በሁለት ፡ ባሕርያት ፤ በእነዚህ ፡ በመለኮ
ትና ፡ በትስብእት ፡ መካከል ፤ መለየት ፤ መለወጥ ፡
መቀላቀል ፤ መደባለቅ ፡ ሳይኖር ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡
እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ገጽ ፤ አንድ ፡ ባሕ
ርይ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ነው ፤ ረቂቅ ፡ መለኮት ፡ ግዙፍ
ሥጋን ፡ ለመሆን ፡ ያለ ፡ መለየት ፤ ያለ ፡ መለወጥ ፡
ነውር ፡ ነቀፋ ፡ ከሌለበት ፡ ከሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ ጋር ፡
ተዋሐደ ፤ ከማይወሰን ፤ ከማይነገር ፡ ተዋሕዶ ፡
በኋላ ፤ መጽሐፍ ፡ ሁለትነትን ፡ አልተናገረም ፤
ሐሰት ፡ ያይደለ ፡ በውነት ፡ መዋቲ ፡ ሥጋን ፡ ተዋ
ሐደ ፤ ከእሱ ፡ ክፍሎ ፡ አልተዋሐደም ፤ ከኃጢ
ጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ የእኛ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡
ፈጸመ ፤ ከእኛም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ።

፲፬ ፤ የእኛ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ ተራበ ፤
ተጠማ ፤ ተኛ ፤ መንገድ ፡ በመሔድ ፡ ደከመ ፤
ይሙት ፤ በቃ ፡ ተፈረደበት ፤ ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤
ተቸነከረ ፤ በፈቃዱ ፡ እስከ ፡ መሞት ፡ ደረሰ ፤ ቅዱ
ሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ፤ የመድኃኒታ
ችን ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ የማይመረመር ፡ ረቂቅ ፡ ምሥ
ጢር ፡ ነው ፤ ባሕርያት ፡ ጥንቱን ፡ እየራሳቸው ፡
መሆናቸውን ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ መዋሐዳቸውን ፡ ያስረ
ዳኻል ።

፲፭ ፤ ድኅነታችን ፡ በዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ተደረገ ፡ ከተባለ ፤
ይህ ፡ ፍጹም ፡ ክሕደት ፡ ነው ፤ ድኅነታችን ፡ በባ
ሕርይ ፡ አምላክ ፡ ተደረገ ፡ እንጂ ፤ አምላክ ፤ ፍጹም
ሰው ፡ መሆኑ ፡ ድንቅ ፤ ረቂቅ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ አም
ላክ ፡ ሰው ፡ የመሆኑ ፡ ነገር ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ከመ
መርመር ፡ በራቀ ፤ ድንቅ ፡ በሚሆን ፡ ተዋሕዶ ፡ ተደ
ረገ ፤ እንደምን ፡ እንደሆነም ፡ ነገሩን ፡ የሚያውቅ ፤
የለም ፤ አምላክ ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ የመሆኑ ፡ ምሥ
ጢር ፡ ዕጹብ ፤ ድንቅ ፡ ነው ፤ ኢሳይያስም ፡ በማይ
መረመር ፤ በማይነገር ፡ ሥራ ፡ ረቂቅ ፡ ድንቅ ፡
ብሎ ፡ ጠራው ፡ እሱም ፡ በሰው ፡ ልቡና ፡ ከመመ
ርመር ፡ የራቀ ፡ ነው ፡ ምትሀት ፤ ኅድረት ፡ ከመሆ
ንም ፡ የራቀ ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፱ ፡ ፮ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፪፲፩ ።

፳፩ ፤ ዘሀሎ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወፈጣሬ ፡ ዓለም ፡ ወእፎኑ ፡ ኮነ ፡ ይደሉ ፡ ይሕምም ፡ እመ ፡ መጽአ ፡ በካልእ ፡ አርአያ ፡ ኀበ ፡ ሕማምነ ፡ ወድካምነ ፡ እመ ፡ ኢተሠገወ ፡ በሥጋ ፡ ዘከማነ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ወኢሐመ ፡ በመለኮት ፡ ወለሊሁ ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ፡ እምቅድመ ፡ ይሡነ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተሠገወ ፡ ወእንበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ንትሜካሕ ፡ በእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዘአግዐዘነ ፡ እምቅኔ ፡ ሞት ፡ መሪር ፡ መጽአ ፡ ወአድኀነነ ፡ እምእደ ፡ አጽራር ፡ ዘውእቶሙ ፡ ሰይጣን ፡ ወሞት ፡ ወኢሐመ ፡ በምት ሀት ፡ ዳእሙ ፡ ሐመ ፡ እሙነ ፡ ዘበአማን ።

፳፪ ፤ ዝንቱ ፡ እምከርሠ ፡ እሙ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ እሙነ ፡ ተዋሐደ ፡ በሥጋ ፡ ሐማሚ ፡ ዘኢየሐምም ፡ ሐመ ፡ ወዘኢይመውት ፡ ጥዕመ ፡ ሞተ ፡ በፈቃዱ ፡ ሰበሰ ፡ አመነ ፡ ካልአ ፡ እምዝንቱ ፡ እም ኢኮነ ፡ ግዑዛነ ፡ እምሕማም ፡ ወእማእሰረ ፡ ሞት ፡ ከመ ፡ ነኪራን ፡ ወርሑቃን ፡ እምጽድቀ ፡ ትንሣኤ ፡ ወክርስቶስ ፡ ተመሰለነ ፡ በኵሉ ፡ ሕማምነ ።

፳፫ ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተንሥአ ፡ እሙነ ፡ እሙታን ፡ ወሰበረ ፡ ኀይሎ ፡ ለጸላኢ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይትናገር ፡ በጥበብ ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ ደቂቅ ፡ ተሳተፍዎሙ ፡ በሥጋ ፡ ወደም ፡ ወውእቱኒ ፡ በዝንቱ ፡ ፍኖት ፡ ወበዝንቱ ፡ አምሳል ፡ ተመሰለ ፡ ከመ ፡ ያብጥል ፡ በሞቱ ፡ ሥልጣነ ፡ ሞት ፡ ዘውእቱ ፡ ሰይጣን ፡ ኢነሥአ ፡ እመላእክት ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ፡ አላ ፡ ነሥአ ፡ እምዘርዐ ፡ አብርሃም ፡ ዘይትዔረየነ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ወዝንቱ ፡ ዘእምእግዝእትነ ፡ ድንግል ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ማርያም ፡ ነሥአ ፡ ሎቱ ፡ እምኔሃ ፡ ሥጋ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ከመ ፡ ይትወከፍ ፡ ቦቱ ፡ ሕማማተ ፡ ሰብአዊ ፡ በፈቃዱ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘያኄብሮ ፡ ወገብረ ፡ ሥርዓተ ፡ መለኮታዊ ፡ ወምግባረ ፡ ሰብአዊ ፡ ወኮነ ፡ ይነብብ ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮቱ ፡ ወለትስብእቱ ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ።

፳፬ ፤ ወአኮ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ ወተናግሮ ፡ ወገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ወኀይላት ፡ ዘኮነ ፡ እምኔሁ ፡ ወሚመ ፡ በእንተ ፡ ሕማማት ፡ ዘቦአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወድካማት ፡ ዘተወክፎሙ ፡ በእንቲአነ ፡ ዘንበውእ ፡ ለከፊለ ፡ ሀላዌያት ፡ እምትስብእት ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ወዘኢይትነገር ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢንከፍል ፡ ቃላተ ፡ ወሕማማተ ፡ በዘሐመ ፡ ቦቱ ፡ እግዚእነ ፡ እስመ ፡ ሎቱ ፡ እሙነ ፡ በኢተፈልጦ ፡ ወተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮቱ ፡ ወሕማም ፡ ወመዊት ፡ ዘይደሉ ፡ ለሀላዌ ፡ ትስብእቱ ።

ዘዮሐንስ ፡ ም ፡ ፪፲፩ ።

፳፩ ፤ ዓለምን ፡ የፈጠረ ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበረ ፡ እሱ ፡ ወደ ፡ ሕማማችን ፤ ወደ ፡ ድካማችን ፡ በሌላ ፡ መልክ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ የምታውቅ ፤ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችውን ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ሥጋን ፡ ባይዋሐድ ፡ ኖሮ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሊታመም ፡ በተገባው ፡ ነበር ፡ እሱ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፤ በመለኮት ፡ ግን ፡ እንዳል ታመመ ፡ እናውቃለን ፤ ሰው ፡ ከመሆኑ ፡ አስቀድሞ ፤ ሰው ፡ ከሆነ ፡ በኋላም ፡ እሱ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፤ ለመራራ ፡ ሞት ፡ ከመገዛት ፡ ነጻ ፡ ስለ ፡ አደረገን ፤ ከጠላቶቻችን ፡ ከሰይጣንና ፡ ከሞት እጅ ፡ ስለ ፡ አዳነን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንመካለን ፡ በእውነት ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ እሱ ፡ በእውነት ፡ ታመመ ፡ እንጂ ፤ በሐሰት ፡ አልታመመም ፤

፳፪ ፤ እሱ ፡ በእናቱ ፡ በእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ በድንግል ፡ ማሕፀን ፡ የሚታመም ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፤ የማይታመመው ፡ ታመመ ፤ የማይሞተው ፡ በፈቃዱ ፡ ሞተ ፤ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ብናምንስ ፡ ከእውነተኛ ፡ ትንሣኤ ፡ እንደ ፡ ተለዩ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ከሞት ፡ ቁራኝነትና ፡ ከሕማም ፡ ነጻ ፡ ባልሆንም ፡ ነበር ፤ ክርስቶስ ፡ በመከራችን ፡ ሁሉ ፡ መሰለን ።

፳፫ ፤ ስለዚህ ፤ በእውነት ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሣ ፤ የጠላት ፡ የዲያብሎስን ፡ ሥልጣን ፡ አጠፋ ፤ ልጆች ፡ ሥጋ ፤ ደም ፡ በመሆን ፡ መሰሉት ፤ እሱም ፡ ሰይጣን ፡ የተባለ ፡ የሞትን ፡ ሥልጣን ፡ በሞቱ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ መሰለን ፡ ብሎ ፡ በጥበብ ፡ የሚናገር ፡ ሐዋርያ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ከእኛ ፡ የነሣውን ፡ ከመላእክት ፡ አልነሣም ፤ የምታወቅ ፤ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችው ፤ በሥራ ፡ ሁሉ እኛን ፡ የሚመስለን ፡ ሥጋን ፡ ከአብርሃም ፡ ባሕርይ ነሣ ፡ እንጂ ፤ ይህም ፡ በጊዜው ፡ ሁሉ ፡ ድንግል ፡ ከምትሆን ፤ አምላክን ፡ ከወለደች ፡ ከእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ የተገኘ ፡ ነው ፤ ግድ ፡ ያለው ፡ ሳይኖር ፡ በፈቃዱ ፡ የሰውን ፡ መከራ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፤ ወልድ ዋሕድ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ ከእሷ ፡ ነሣ ፤ መለኮታዊ ፡ ሥርዓትን ፤ ሰብአዊ ፡ ሥራን ፡ ሠራ ፤ ሳይለይ ፡ ለአምላክነቱ ፡ ለሰውነቱ ፡ የሚገባውን ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

፳፬ ፤ በእሱ ፡ የተፈጸመውን ፡ ተአምራትና ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ ማድረጉን ፤ አነጋገሩን ፤ ሥራውን ፤ ወይም በእሱ ፡ የተፈጸሙ ፡ ሕማማትን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የተቀበላቸውን ፡ ድካማትን ፡ ምክንያት ፡ አድርገን ፡ ከማይነገር ፤ ከማይመረመር ፡ ተዋሕዶ ፡ በኋላ ፤ ባሕርያትን ፡ ወደ ፡ መከፈል ፤ መለኮትን ፡ ከትስብእት ፡ ወደ ፡ መለየት ፡ የምንገባ ፡ አይደለም ፤ ስለዚህም ፡ ጌታችን ፡ የተቀበለውን ፡ መከራና ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አንከፍልም ፤ ለመለኮት ፡ የሚቻል ፡ ተአምራት ፡ ማድረግ ፤ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ መሥራትም ፡ ቢሆን ፡ ለሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ የሚስማማ ፡ ሕማም ፤ ሞትም ፡ ቢሆን ፡ ባለመለየት ፡ በእውነት ፡ ለእሱ ፡ ገንዘቦቹ ፡ ናቸውና ።

## ዘሐቢብ ፡ ም ፡ ፻፲፭ ።

### ምዕራፍ ፡ ፻፲፭ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ ይቤ ፡ ሐቢብ ፡ ዘውእቱ ፡ ፍቁር ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ ተክሪት ፡ ወወይከኒ ፡ ወአበሪዳ ፡ በውስተ ፡ መልእክቱ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ በደቡብ ፡ ወበምዕራብ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔርሰ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ በሀላዌሁ ፡ እንዘ ፡ ፩ዱ ፡ ፫ቱ፡ ወእንዘ ፡ ፫ቱ ፡ ፩ዱ ፡ ወ፩ዱ ፡ ዘእምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ወልድ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበቡ ፡ ወጸዳለ ፡ ብርሃኑ ፡ አመ ፡ አልጸቀ ፡ ዘመን ፡ ወረደ ፡ እምሰማይ ፡ በሥምረተ ፡ አቡሁ ፡ ወበፈቃደ ፡ ርእሱ ፡ ወተሠገወ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ነሥአ ፡ እምኔሃ ፡ ሥጋ ፡ ወአስተርአየ ፡ ቦቱ ፡ ማእከሌነ ፡ ተፈጸመ ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ፡ ውስቴቱ ፡ ወተነብየ ቶሙ ፡ በእንቲአሁ ።

፪ ፤ ወሥጋ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔሃ ፡ አኮ ፡ በምትሀት ፡ ወአኮ ፡ በተዐርቆ ፡ እምኔሁ ፡ ዘከመ ፡ ይብሉ ፡ ሰብእ ፡ ስሑታን ፡ ወባሕቱ ፡ ነሥአ ፡ ሥጋ ፡ ፍጹመ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ መሀረነ ፡ መምህረ ፡ ጽድቅ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፡ በጥንተ ፡ መጽሐፉ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ወርኢነ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ከመ ፡ ስብሐተ ፡ ፩ዱ ፡ ዋሕድ ፡ ለአቡሁ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።

### ክፍል ፡ ፪ ።

፫ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በዝንቱ ፡ ድርሳን ፡ እምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስሰ ፡ መንጦላዕተ፡ መለኮት፡ ዘውእቱ ፡ ሥጋሁ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ።

### ክፍል ፡ ፫ ።

፬ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በመልእክቱ ፡ ሣልሲት ፡ እምኮቱ ፡ መልእክታት ፡ ዘተናገረ ፡ ባቲ ፡ በእንተ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ወትሥጉት ፡ ንሕነሰ ፡ ተናገርነ ፡ በካልእ ፡ መካን ፡ እምዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ተሰብአ ፡ ወባሕቱ ፡ ተብህለ ፡ ሞተ ፡ በሥጋሁ ፡ ወአኮ ፡ በመለኮቱ ። ወሞቱሰ ፡ በሥጋሁ ፡ ተፈልጠተ ፡ ነፍሱ ፡ እምሥጋሁ ፡ ዘተፈጥረት ፡ ወመለኮትሰ ፡ ኢተፈልጠ ፡ እምነፍሱ ፡ ወኢእምሥጋሁ ፡ አላ ፡ ይትዋሐድ ፡ ዘልፈ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በከመ ፡ ነገርነ ፡ ወንቤ ።

## ዘሐቢብ ፡ ም ፡ ፻፲፭ ።

### ምዕራፍ ፡ ፻፲፭ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፤ ይኸውም ፡ የተወደደ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በተክሪት ፡ በወይከኒና ፤ በአበሪዳ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ የተሾመ ፡ ሐቢብ ፡ ለደቡብና ፡ ለምዕራብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ሲሆን፡ ሦስት ሦስት ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃሉ ፤ ጥበቡ ፤ የባሕርዩ ፡ መታወቂያ ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፤ አንዱ ፡ አካል ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፤ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ በአባቱ ፡ ፈቃድ ፤ በራሱ ፡ ፈቃድ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል፡ ማርያም ፡ ነፍስን ፤ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፤ በነሣው ፡ ሥጋም ፡ በመካከላችን፡ ተገለጠ ፤ ስለ ፡ እሱ ፡ የተናገሩት ፡ የነቢያት ፡ ቃል ፡ በእሱ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ተፈጸመ ።

፪ ፤ ከእሷ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ግን ፤ በሐሰት ፡ አይደለም ፤ የካዱ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ በኅድረት ፡ አይደለም ፤ እሱ ፡ ፍጹም ፡ ሥጋን ፡ ነሣ ፡ እንጂ ፤ የውነት ፡ መምህር ፡ ወንጌላዊ ፡ ዮሐንስ ፡ በመጽሐፉ ፡ መጀመሪያ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ፤ በእኛም ፡ አደረ ፤ ለአባቱ ፡ አንድ ፡ እንደሆነ ፡ ልጅ ፡ ያለ ፡ ክብሩን ፡ አየንለት ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ አስተማረን ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።

### ክፍል ፡ ፪ ።

፫ ፤ ዳግመኛ ፤ በዚህ ፡ ድርሳን ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ክርስቶስስ ፡ መለኮትን ፡ ተገልጦ ፡ አየን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ከእኛ ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤

### ክፍል ፡ ፫ ።

፬ ፤ ዳግመኛም ፤ ከሦስቱ ፡ መልእክታት ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴንና ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ በተናገረበት ፡ በሦስተኛው ፡ መልእክት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እኛ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ፡ መጽሐፍ ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ተናግረናል ፤ ነገር ፡ ግን ፤ በመለኮቱ ፡ ያይደለ ፡ በሥጋው ፡ ሞተ ፡ ተብሎ ፡ ተነገረ ፤ በሥጋው ፡ ሞተ ፡ መባሉም ፡ ነፍሱ ፡ ከተፈጠረች ፡ ከሥጋው ፤ መለየቷ ፡ ነው ፤ መለኮት ፡ ግን፡ ከሥጋውም ፤ ከነፍሱም ፡ አልተለየም ፤ እንደ ፡ ተናገርን ፤ ከሥጋ ፤ ከነፍስ ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ ይኖራል ፤ እንጂ ።

## ቃለ ፡ ግዘት ፡ ም ፡ ፻፲፰ ።

### ምዕራፍ ፡ ፻፲፰ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩፤ ድርሳን ፡ ዘተናገረ ፡ ባቲ ፡ ዮልዮስ ፡ ርእሰ ፡ ኤጲስ፡ ቆጶሳት ፡ ዘሮሜ ፡ ዘኮነ ፡ ስምዐ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ በውስተ ፡ መጽሐፉ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወአውገዘ ፡ ባቲ ፤ እመቦ ፡ ዘይቤ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘነሥእዎ ፡ እምኀበ እግዚአብሔር ፤ ወእግዚአብሔርኒ ፡ ኀደረ ፡ በኢየሱስ ፡ ዘውእቱ ፡ እማርያም ፡ ወከመ ፡ ውእቱ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ ፍጹማን ፡ ኢኮኑ ፡ ፩ደ ፡ ኅቡረ፡ ያእምር ፡ እንከ ፡ ዘይቤ ፡ ከመዝ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ነኪር ፡ እምተስፋ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘቦቱ ፡ ኮነ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ወኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ዘውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በከመ ፡ መሀሩነ ፡ ዮሐንስ ፡ ወጳውሎስ ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

### ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

፪፤ እመቦ ፡ ዘኢየአምን ፡ በብእሲ ፡ ዘውእቱ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አምላክ ፡ ለባሴ ፡ ሥጋ ፤ ወለሊሁ ፡ ዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወውእቱ ፡ አምላክ ፡ ህልው ፡ እምቀዲሙ ፡ ወኢተወለጠ ፡ መለኮቱ ፡ ለከዊነ ፡ ሥጋ ፡ ሐማሚ፡ ወጉዘ ፡ ለይኩን ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩—፲፰ ።

### ክ ፍ ል ፡ ፫ ።

፫፤ እመቦ ፡ ዘይብል ፡ ከመ ፡ ሥጋ ፡ መድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢኮነ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ማርያም፤ አላ ፡ እምሰማይ ፡ ውእቱ ፡ ወይብሎ ፡ ለፍጡር ፡ ኢተፈጥረ ፤ ወውእቱ ፡ ኮነ ፡ እምኀበ ፡ ኢሀልዎ ፤ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ ወዘሂ ፡ ይብል ፡ ዓዲ ፡ በእንተ ፡ ሥጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋ ፡ አምላክ ፡ በእንተ ፡ ዘተዋሐደ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘኢተፈጥረ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ንስግድ ፡ ሎቱ ፡ ምስለ ፡ ሥጋሁ ፡ አሐተ ፡ ስግደተ ፡ ወውእቱ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ ዘኢተፈጥረ ፡ ወኢኮነ ፡ ፪ተ ፡ ዘሰ ፡ የአምን ፡ ከመዝ ፡ ብፁዕ ፡ ውእቱ ።

### ክ ፍ ል ፡ ፬ ።

፬፤ ወለነሰ ፡ ለክርስቶሳውያን ፡ ሃይማኖትነ ፡ ከመ ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ ሐዋርያዊ ፡ ውእቱ ፡ በእንተ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ መለኮት ፡ ዘበአማን ፡ ወአሐቲ ፡ ስግደት ፡ ወ፩ዱ ፡ ስባሔ ወ፩ዱ ፡ ክብር ፡ ወአሐቲ ፡ ሥልጣን ፡ ወ፩ዱ ፡ ዕበይ ፡ ወአሐቲ ፡ ሥምረት ፡ ወ፩ዱ ፡ ፈቃድ ፡ ዘአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ወዘሰ ፡ ያበውእ ፡ መለኮተ ፡ ካልአ ፡ አው ፡ ያመጽእ ፡ ስባሔ ፡ ካልአ ፡ እምቃላተ ፡ ሱራፌል ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ «ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር» እግዚአ ፡ ኀይላት ፡ ምሉዕ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ ፡ ስብሐቲከ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፩—፱ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፮ ።

## ቃለ ፡ ግዘት ፡ ም ፡ ፻፲፰ ።

### ምዕራፍ ፡ ፻፲፰ ፡ ክፍል ፡ ፩ ።

፩፤ ጢሞቴዎስ ፡ በመጀመሪያ ፡ መጽሐፉ ፡ መስክሮ ፡ ያወገዘባት ፤ የሮም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዮልዮስ ፡ የተናገራት ፡ ድርሳን ፡ ይህች ፡ ናት ፤ ከእግዚአብሔር፡ የተሾመ ፡ ዕሩቅ ፡ ብሲ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከማርያም ፡ በተወለደው ፡ አደረ ፤ ፍጹማን ፡ የሚኾኑ ፡ ሁለቱ ፡ ባሕርያትም ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አልኾኑም ፡ የ ሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፤ ይህን ፡ እንዲህ፡ የሚል ፤ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፤ ሥራውን ፡ ሁሉ የሠራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከሚሰጠው ፡ ተስፋ፡ የተለየ ፡ እንደኾነ ፡ ይወቅ ፤ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፤ ዮሐንስና ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ አስተማሩን ። ዕብ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

### ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

፪፤ ከእመቤታችን ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ የተወለደው፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡ እንደሆነ ፤ ከአብ ፡ ጋር እኩል ፡ ትክክል ፡ እንደሆነ ፤ በቅድምና ፡ የነበረ ፡ አምላክ ፡ እንደኾነ ፤ መለኮቱም ፡ የሚታመም ፡ ሥጋን ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ እንዳልተለወጠ ፡ የማያምን፡ ሰው ፡ ቢኖር ፤ ውጉዝ ፡ ይሁን ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩—፲፰ ።

### ክ ፍ ል ፡ ፫ ።

፫፤ መድኃኒታችን ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ከሰማይ ፡ የመጣ ነው ፡ እንጂ ፡ ከማርያም ፡ የተገኘ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፤ ፍጡሩንም ፡ አልተፈጠረም ፡ የሚለው ፡ እንደ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉም ፡ ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር፡ መጣ ፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይኹን ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ነሣው ፡ ሥጋም ፡ ፍጡር ፡ ያይደለ ፡ አምላክን ፡ ስለ ፡ ተዋሐደ ፡ የአምላክ ፡ ሥጋ ነው ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃልን ፡ ከሥጋው ሳንለይ ፡ አንዲት ፡ ስግደትን ፡ ልንሰግድለት ፡ ይገባናል ፤ እሱ ፡ ያልተፈጠረ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሁለት ፡ አይደለም ፡ የሚል ፤ እንዲህም ፡ የሚያምን ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

### ክ ፍ ል ፡ ፬ ።

፬፤ ለእኛ ፡ ለክርስቲያን ፡ ግን ፤ ስለ ፡ አብ ፡ ስለ ፡ ወንድ ፤ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት፡ ትምህርት ፡ ሥርዓት ፡ የምናምነው ፡ ሃይማኖታችን ፤ በውነት ፡ አንድ ፡ መለኮት ፡ አንድ ፡ ስግደት ፤ አንድ ፡ ምስጋና ፤ አንድ ፡ ክብር ፤ አንዲት፡ ሥልጣን ፤ አንድ ፡ ጌትነት ፤ አንዲት ፡ መሻት ፤ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ የአብ ፤ የወልድ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሌላ ፡ አምላክን ፡ የሚሰብክ ፤ የመላእክት ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ፤ ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፤ ተብለህ ፡ የምትመሰገነው ፡ ምስጋና ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ሙሉ ፡ ነው ፤ እያሉ ፡ ሱራፌል ፡ ከሚያመሰግኑት ፡ ምስጋና ፡ የተለየ ፡ ሌላ ፡ ምስጋና ፡ የሚያመጣ ፡ ውጉዝ ፡ ይኹን ። ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፩—፱ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፮ ።

ቃለ ፡ ግዘት ፡ ም ፡ ፶፬ ። ም ፡ ፶፭

## ክፍል ፡ ፱ ።

፲፫ እመቦ ፡ ዘይቤ ፡ ከመ ፡ ቃል ፡ ይትኤዘዝ ፡ ለሥጋ ፤ ወመለኮትሰ ፡ ዕሩቅ ፡ እምሥጋ ፡ ወፍሉጥ ፡ ወኢተዋሐደ ፡ ምስሌሁ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ።

## ክፍል ፡ ፲ ።

፲፬ እመቦ ፡ ዘይቤ ፡ ከመ ፡ ሥጋሁ ፡ አውረደ ፡ እምሰማይ ፤ ወአኮ ፡ እምዝየ ፡ እምኔነ ፡ ወባሕቱ ፡ ይትሌዐል ፡ እምኔነ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ።

## ክፍል ፡ ፲፩ ።

፲፭ እመቦ ፡ ዘይቤ ፡ ከመ ፡ ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ምትሀት ፡ ውእቱ ፡ ወለትሥጉትሂ ፡ አልቦቱ ፡ ልቡና ፡ ወአእምሮ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ያድኅን ፡ ምንተኒ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ።

## ክፍል ፡ ፲፪ ።

፲፮ እመቦ ፡ ዘይብል ፡ ከመ ፡ ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዘይትቄደስ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ኢኮነ ፡ እሙነ ፡ ሥጋሁ ፡ አላ ፡ ምትሀት ፡ ውእቱ ፡ ወኢይቤ ፡ በአማን ፡ ሥጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ወኢኮነ ፡ ምትሀተ ፡ ወለሊሁ ፡ ቅዱስ ፡ ሐማሚ ፡ በሥጋ ፡ ኢሐማሚ ፡ ወኢመዋቲ ፡ በመለኮቱ ፡ ኢየሐምም ፡ ወኢይመውት ፡ ወሀቤ ፡ ሕይወት ፡ ወቀዳሲሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይነሥእዎ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ።

## ክፍል ፡ ፲፫ ።

፲፯ እመቦ ፡ ዘይቤ ፡ ከመ ፡ ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ሀለወ ፡ ምስሌሁ ፡ እምቀዲሙ ፡ ዕሩየ ፡ ምስለ ፡ መለኮት ፡ ወወረደ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፤ ወአኮ ፡ እማርያም ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፤ ተፈጸመ ፡ ቃለ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ በሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሜን ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፭ ።

፩ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ፲ቱ ፡ ወ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ እንተ ፡ ዘነበበ ፡ ባቲ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ወተጽሕፈት ፡ ዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ በኤፌሶን ፡ እምጉባኤ ፡ ቅዱስ ።

ቃለ ፡ ግዘት ፡ ም ፡ ፶፬ ። ም ፡ ፶፭ ።

## ክፍል ፱ ።

፲፫ ሥጋ ፡ ለቃል ፡ ይታዘዛል ፤ መለኮትም ፡ ከሥጋ ፡ ፈጽሞ ፡ የተለየ ፡ ነው ፤ ከእሱም ፡ ጋር ፡ አልተዋሐደም ፤ የሚል ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይኹን ።

## ክፍል ፡ ፲ ።

፲፬ ከሰማይ ፡ ሥጋን ፡ ይዞ ፡ መጣ ፤ ከምድር ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ፡ የተገኘ ፡ አይደለም ፤ ከእኛ ፡ ይበልጣል፤ የሚል ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይዙን ።

## ክፍል ፡ ፲፩ ።

፲፭ ክርስቶስ ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ምትሀት ፡ ነው ፤ ለተዋሐደው ፡ ሥጋም ፡ አእምሮና ፡ ልብ ፡ የለውም ፤ ምንም ፡ ምን ፡ ሊያድን ፡ አይችልም ፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይኹን ።

## ክፍል ፲፪ ።

፲፮ በኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሠዋው፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋው ፡ ምትሀት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ሥጋው ፡ አይደለም ፡ የሚል ፤ በውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤ ምትሀትም ፡ አይደለም ፤ እሱ ፡ በሥጋ ፡ የሚታመም ፤ በመለኮት ፡ ግን ፡ ሕማም ፤ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፤ እሱ፡ አይታመምም ፤ አይሞትም ፤ ሕይወትን ፡ የሚያድል ፤ የሚቀበሉትንም ፡ የሚያከብራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ የማይል ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይሁን ።

## ክፍል ፡ ፲፫ ።

፲፯ ክርስቶስ ፡ የተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ ከመለኮት ፡ ጋር፡ ከጥንት ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ አብሮ ፡ ኖሮ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ መጣ ፤ ከማርያም ፡ የተገኘ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይኹን ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ተፈጸመ ፡ አሜን ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፭ ።

፩ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ የተናገራት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ቃለ ፡ ግዘት፡ ይህች ፡ ናት ፤ ይህቺም ፡ በኤፌሶን፡ በተደረገው ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤ ፡ ተጻፈች ።

ቃለ ፡ ግዘት ፡ ም ፡ ፻፷፩ ።

፲፪ ፤ ወእለሰ ፡ ኢየአምኑ ፡ ከመዝ ፡ እሎንተ ፡ ቃላተ ፡ ይክፍልዎ ፡ ለ፩ዱ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ በበይናቲሆሙ ፡እሉ ዘኮኑ ፡ ፩ደ ፡ በተዋሕዶ ፡ እሙን ፤ ወይሁቡ ፡ ክብረ ፡ ዘከመ ፡ ይትፋለስ ፡ ኵሉ ፡ ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ እምሀላዌ ያት ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ወባሕቱ ፡ ንሕነሰ ፡ መሢሓው ያን ፡ ንብል ፡ ገሃደ ፡ በሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወጽድ ቅት ፡ ወንጽሕት ፡ ከመ ፡ እሉ ፡ ነኪራን ፡ እምኔሁ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ከመዝ ። ወሶበሂ ፡ ተሰምየ ፡ ሐዋርያ ፡ አው ፡ ተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ቅቡዕ ፡ውእቱ ፡ ወተሰምየ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ኢንኀፍር ፡ ንሕነ ፡ እምሥርዓተ ፡ መድኀን ፤ ወንብል ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ፡ አምላክ ፡ቃል ፡ ለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ዘመጽአ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ከማነ ፡ ተሰ ምየ ፡ ሐዋርያ ፡ ወተቀብዐ ፡ ምስሌነ ፡ ከመ ፡ሥር ዓተ ፡ ትስብእት ።

፲፫ ፤ ወዘሂ ፡ ኮነ ፡ ከማነ ፡ ውእቱኒ ፡ ዓዲ ፡ ኢያስተሐ ቀረ ፡ ዘዚአነ ፡ ውእቱ ፡ ህልው ፡ ወኢይትፈለጥ ፡ እንከ ፡ እምትስብእቱ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓት ፡ ወኢይትዌለጥ ፡ እምዐቅመ ፡ ሰብእናሁ ፡ ወኢይፈልስ ፡ ዓዲ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮት ፡ ክብርት ፡ ወልዕልት ፡ ምንተኒ ፡ ለግሙራ ፡ አላ ፡ ውእቱሰ ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፡ ሠምረ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ በፈ ቃዱ ፡ ወውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አኃዜ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ዘሰማያውያንሂ ፡ ወምድራውያን ።

<u>ክፍል ፡ ፫ ።</u>

፲፬ ፤ እመቦ ፡ ዘይከፍል ፡ ህላዌያተ ፡ ወአካላተ ፡ እንተ ፡ ዘ፩ዱ ፡ እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፤ አው ይሬሲ ፡ አካለ ፡ ክርስቶስ ፡ ፪ተ ፡ እምድኅረ ፡ ተዋ ሕዶ ፡ ወይብል ፡ እስመ ፡ ተላጽቆቶሙ ፡ ተላጽቆተ ፡ ክብር ፡ ወሰላም ፡ ወኀይል ፡ ውእቱ ፤ ወኢኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ተዋሕዶ ፡ ህላዌ ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ወኢ ውላጤ ፡ ውኁዘ ፡ ለይኩን ። ፍካሬ ፡ እስመ ፡ ለም ሥጢረ ፡ ሥርዓትሰ ፤ እንተ ፡ ዘዋሕድ ፡ ንሕነ ፡ ንሌብዎ ፡ በስብሐት ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ወንብል፡ከመ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ፩ደ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ዘቦቱ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወለባዊት ፡ ወማሕየዊት ፡ ዘውእቱ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ እንተ ፡ ዘአብ ፡ ወ፩ዱ ፡ ውእቱ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ቀዳ ማዊ ፡ ዝንቱ ፡ ዘይደሉ ፡ ከመዝ ፡ ንበል ፡ በእንቲ አሁ ።

ቃለ ፡ ግዘት ፡ ም ፡ ፻፷፩ ።

፲፪ ፤ እንዲህ ፡ እነዚህን ፡ ቃላት ፡ የማያምኑ ፡ ግን ፤አንዱን ለያይተው ፡ ከሁለት ፡ ይከፍሉታል ፤ ባሕርያት ፤በእ ውነተኛ ፡ ተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ የኾኑ ፡ ናቸው ፤ ከባሕ ርያት ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ሁሉ ፡ በአንዱ ፡ እንደ ፡ አደረ ፡ አድርገው ፡ መበላለጥን ፡ ይሰጣሉ ፤ እኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፤ በቀናች ፤ በተረዳች ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንተን ፡ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ እነዚህ ፤ ከእሱ ፡ የተለዩ፡ እንደኾኑ ፡ እንናገራለን ። ሐዋርያ ፡ ቢባል ፤ ወይም ፡ ክርስቶስ ፤ እንደሆነ ፡ ቢነገር ፤ የአምላክ ፡ ልጅም ፡ ቢባል ፤ መድኀን ፡ ክርስቶስ ፡ በፈጸመው ፡ ሥር ዓት ፡ እኛ ፡ አናፍርም ፤ ከአብ ፡ ተወልዶ ፤ ሰው ፡ የኾነ ፡ እሱ ፡ አምለክ ፡ ቃል ፡ እንደኾነ ፡ እንናገራ ለን ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ ሰውም ፡ ቢኾን ፡ ሐዋርያ ፡ ተባለ ፤ ለሰውነትም ፡ እንደሚገባ ፡ እንደኛ ፡ መሢሕ ፡ ተባለ ።

፲፫ ፤ ዳግመኛም ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ እሱ ፡ የእኛን ፡ ባሕርይ ፡ ንቆ ፡ አልተወም ፤ እሱ ፡ በባሕ ርዩ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፤ ስለ ፡ ተዋሕደ ፤ ከእኛ ፡ ከነሣው ፡ ሥጋ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይለይም ፤ ሰው ፡ ከመኾንም ፡ አይለወጥም ፤ ልዕልት ፤ ክብ ርት ፡ ከምትኾን ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮትም ፡ ለዘለዓ ለም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አይፋለስም ፤ እሱስ ፡ ቀዳማዊ ፡ ነው ፤ በፈቃዱም ፡ ወዶ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፤ ሰማያውያን ፤ ምድራውያንም ፡ ቢኾኑ ፡ ፍጥረትን ፡ ሁሉ ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ አምላክ ፡ እሱ ፡ ነው ።

<u>ክፍል ፡ ፫ ።</u>

፲፬ ፤ የአንዱን ፡ የጌታችንን ፡ የክርስቶስን ፡ ባሕርይ ፤ አካል ፡ ከሁለት ፡ የሚከፍል ፡ ቢኖር ፤ ወይም ፡ ከተ ዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ የክርስቶስን ፡ አካል ፡ ሁለት ፡ የሚ ያደርግ ፤ አንድነታቸውም ፡ የክብር ፤ የፍቅር ፡ የኀ ይል ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ይህ ፡ አንድነት ፡ መለየት ፤ መለወጥ ፡ የሌለበት ፡ የባሕርይ ፡ ተዋሕዶ ፡ አይደ ለም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይኹን ። ትርጓሜ ፤ የክርስቶስን ፡ የተዋሕዶውን ፡ ምሥጢር ፡ በማይመረመር ፡ ግብር ፡ እንደኾነ ፡ እናውቀዋለን ፤ አሁንም ፡ ለባዊት ፤ ነባቢት ፤ ሕይወት ፡ ነፍስ ፡ከአ ለችው ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ኾነ ፡ እንላለን ፡ ይኸውም ፡ ከአብ ፡ የተገኘ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ስለእሱ ፡ እንዲህ ፡ ብለን ፡ ልንናገርለት ፡ የሚገባን ይህ ፡ በቅድምና ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ ወልድ ፡ ኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መቼም ፡ መች ፡ አንድ ፡ ነው ።

ቃለ ፡ ግዘት ፡ ም ፡ ፻፳፩ ።

፳ ፤ ወሶበሂ ፡ ናዜክር ፡ እንተ ፡ ዘትስብእቱ፡ ንሐ ሊ ፡ ዓዲ ፡ በእንተ ፡ መለኮቱ ፡ ወትስብእትሂ ፡ ሎቱ ፡ ውእቱ ፡ ወሶበሂ ፡ ንትናገር ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ነአ ምን ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ ወተፈጸመ ፡ ቃላቲሁ ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ መሢሕ ፡ ውእቱ ፡ ወ፩ዱ ፡ ወልድ ፡ ዘበአማን ፡ ወእለሰ ፡ ያመጽኡ ፡ ፪ተ ፡ ህላዌያተ ፡ ወ፪ተ ፡ አካላተ ፡ ይሔ ልዩ ፡ ከመ ፡ ፪ቱ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ ንሕነ ፡ ዕጓለ ፡ ሕመሕያው ፡ ኢይትከሀል ፡ ይፍልጡነ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ ወኢኀበ ፡ ፪ቱ ፡ አካላተ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ንሕነ ፡ እምነ ፡ ነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ዳእሙ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ንሕነ ፡ ከማሁኬ ፡ ዓዲ ፡ ዐማኑኤል ፡ አምላክነ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ ትስብእቱ ፡ ወ፩ዱ፡ እግዚእ ፡ አሐዱ ፡ ወልድ ፡ ወቃልሂ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ ፍጹመ ፡ በ፩ዱ ፡ ገጽ ፡ ወ፩ዱ ፡ አካል ፡ ወ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ዘእንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ለግሙራ ፡ ንብሎ ፡ ሰብአ ፡ በእንተ ፡ ትስብእቱ ፡ ወአምላከ ፡ በእንተ ፡ መለኮቱ ፡ ወተወልዶቱ ፡ እምአብ ፤ ወበእንተ ፡ ገቢሮቱ ፡ ኃይላተ ፡ ወመንክራተ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ወእለሰ ፡ ይፈልጥዎ ፡ ወይሬስይዎ ፡ ብእሴ ፡ ዕሩቀ ፡ በባሕቲቱ ፡ በዐቅሙ ፡ ወዓዲ ፡ ሀሎ ፡ ወልድ ፡ ካልእ ፡ ውጉዛነ ፡ ለይኩኑ ።

ክፍል ፡ ፳ ።

፳፩ ፤ እመቦ ፡ ዘይትሀበል ፡ ወይብል ፡ እስመ ፡ ክርስ ቶስ ፡ ብእሲ ፡ ጸዋሬ ፡ አምላክ ፡ ወኢኮነ ፡ አምላከ ፡ ጽድቅ ፡ ዘበአማን ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘበአማን ፤ ወቃልሂ ፡ ሥጋ ፡ ኢኮነ ፡ ወኢተሳተፈ ፡ ደመ ፡ ወሥጋ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ። ፍካሬ ፡ ይቤ ፡ ብፁዕ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ አኮ ፡ በተፋልሶ ፡ እምህላዌሁ ፡ ኀበ ፡ ሥጋ ፡ በከመ ፡ ንቤ ፡ ቅድመ ፤ ውእቱሰ ፡ ኢይትዌለጥ ፡ እስመ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ አላ ፡ ዳእሙ ፡ ተሳተፈነ ፡ በሥጋ ፡ ወደም ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ ከማነ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩—፲፬ ። ሚል ፡ ፫ ፡ ፮ ።

፳፪ ፤ ወልማዶሙ ፡ ለመጻሕፍት ፡ ማሕየውያን ፡ ይሰም ይዎ ፡ ለብእሲ ፡ ሥጋ ፡ እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውእቱ ፡ ወዅሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ርእየ ፡ አድኅኖቶ ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ ወባሕቱ ፡ በዓለ ፡ ሃይማኖት ፡ ርቱዕት ፡ ዘውእቱ ፡ ንስጥሮስ ፡ ወእሊአሁ ፤ ወእለ ፡ ይትአ መኑ ፡ ከማሁ ፡ በአድልዎ ፡ ይብሉ ፡ ዕሩቅ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋ ፡ እምቃል ፡ ወኢይትአመኑ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ እሙነ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡ ከማነ ፡ ወነበረ ፡ በዘሀለወ ፡ ቦቱ ።

ቃለ ፡ ግዘት ፡ ም ፡ ፻፳፩ ።

፳ ፤ ሰው ፡ የመኾኑን ፡ ነገር ፡ በምንናገርበት ፡ ጊዜም ፡ የአምላክነቱን ፡ ነገር ፡ እንናገራለን ፤ ሥጋም ፡ ገን ዘቡ ፡ ነው ፤ አምላክ ፡ እንደኾነ ፡ ብንናገርም ፤ እሱ ፡ ጥንቱን ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደኾነ ፤ ኋላም ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ እናምንበታለን ፤ አንድ ፡ ክርስቶስ ፤ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ ወልድ ፡ እንደኾነ ፡ የተናገረው ፡ ነገሩ ፡ ተፈጸመ ፤ ሁለት ፡ ባሕርይ ፤ ሁለት ፡ አካል ፡ የሚሉ ፡ ግን ፤ ሁለት ፡ እንደኾነ ፡ ይናገራሉ ፤ እኛ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንባላ ለን ፡ እንጂ ፤ ከነፍስ ፤ ከሥጋ ፡ ስለ ፡ ተፈጠርን ፡ እኛን ፡ ሰዎችን ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ አካል ፤ ወደ ፡ሁለት ባሕርይ ፡ ሊከፍሉን ፡ እንዳይቻል ፤ እንዲሁ ፡ ዐማኑ ዔል ፡ አምላካችን ፡ ከሥጋው ፡ የማይለይ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ወልድ ፡ አንድ ፡ ገዥ ፡ ነው ፤ ቃልም ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ያለ ፡ መለየት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ አካል ፤ አንድ ፡ ገጽ ፡ በመኾን ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ሰው ፡ ስለኾነ ፡ ሰው ፡ እንለዋለን ፤ አም ላክ ፡ ስለ ፡ መኾኑ ፤ ከአብም ፡ ስለ ፡ መወለዱ ፤ የማይ መረመር ፤ ድንቅ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራትን ፡ በማድረጉ፡ አምላክ ፡ እንለዋለን ፤ በአካሉ ፡ በብቻው ፡ የተለየ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አድርገው ፡ የሚለዩት ፤ ዳግመኛ ፡ ሁለተኛ ፤ ወልድ ፡ አለ ፡ የሚሉትም ፡ ውጉዛን ፡ ይኹኑ ።

ክፍል ፡ ፳ ።

፳፩፤ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ያደረበት ፤ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ እን ደኾነ ፤ እሱም ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንዳይደለ ፤ ቃልም፡ ሥጋን ፡ እንዳልኾነ ፤ ነፍስን ፤ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ እንደ አልተዋሐደ ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ይኹን ። ትርጓሜ ፤ የተመሰገነ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፤ አለ ፤ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተና ገርን ፡ በባሕርዩ ፡ ሥጋን ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ ተለውጠ ፡ አይደለም ፤ እሱ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ አይለወጥም ፤ ነፍስን ፡ ሥጋን ፡ በመዋሐድ ፡ መሰለን ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ ሰውም ፡ ኾነ ፡ እንጂ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩—፲፬ ። ሚል ፡ ፫ ፡ ፮ ።

፳፪ ፤ ድኅነት ፡ የሚገኝባቸው ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ልማዳቸው ፡ ነውና ፡ ሰውን ፡ ሥጋ ፡ ብለው ፡ ይጠ ሩታል ፤ ሥጋው ፤ ደማዊ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብ ሔርን ፡ ትድግና ፡ አየ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎአልና፤ ሃይማ ኖተ ፡ ክፉ ፡ ንስጥሮስና ፡ ወገኖቹ ፤ እንደ ፡ እሱም ፡ በሐሰት ፡ የሚታመኑ ፡ ሥጋ ፡ ከቃል ፡ የተለየ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በእውነት ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡እንደኾነ በአምላክነቱም ፡ ጸንቶ ፡ እንደኖረ ፡ አያምኑም ።

## ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፬ ።

### ክ ፍ ል ፡ ፪ ።

፲፬ ፡ እመልእክተ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ኀበ ፡ ነገሥት ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወአኮ ፡ ብእሲ ፡ ዕሩቅ ፡ በባሕቲቱ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአሁ ፡ ረድኡ ፡ በጥበብ ፡ ወበለብዎ ፡ ልብ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስሰ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ በፈቃዱ ፡ ወኢሐመ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወለሊሁ ፡ ርሑቅ ፡ እምኵሉ ፡ ሕማም ፡ ወነኪር ፡ እምኔሁ ፡ ሕማም ፡ ወባሕቱ ፡ ሐመ ፡ ይእዜ ፡ በሥጋሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ በከመ ፡ ተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ወውእቱ ፡ ኢሐማሚ ፡ በህላዌሁ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወከመዝ ፡ ነአምሮ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ተቀብዐ ፡ ከመ ፡ ሥርዓተ ፡ ትስብእት ፡ ወዳእሙ ፡ ውእቱ ፡ ዘይቀብዕ ፡ ርእሶ ፡ በመንፈሱ ፡ ባሕቲቱ ።

፲፭ ፡ ይቤ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ነባቤ ፡ መለኮት ፡ በመልእክቱ ፡ ኀበ ፡ አቅላንድዮስ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐማሚ ፡ ውእቱ ፡ በሥጋ ፡ ወኢሐማሚ ፡ በመለኮት፡ ለሊሁ ፡ ይትገመር ፡ በሥጋ ፡ ወኢይትገመር ፡ በመንፈስ ፡ ወውቱሰ ፡ ከመ ፡ ሰማያዊ ፡ ወውእቱ ፡ ምድራዊ ፡ ያስተርኢ ፡ ወኢያስተርኢ ፡ ይትሌበው ፡ ወኢይትሌበው ፡ ወባሕቱ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ፍጹም ፡ ብእሲ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወውእቱ ፡ ሐደሰ ፡ ፍጥረቶ ለብእሲ ፡ ዳግመ ፡ ዝንቱ ፡ ዘወድቀ ፡ በኃጢአት ።

፲፮ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ መምህር ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ወርእሰ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ዐምደ ፡ ሃይማኖት ፡ በድርሳኑ ፡ እንዘ ፡ ያወሥእ ፡ ለአቡሊናርዮስ ፡ ዓላዊ እስመ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔርሰ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ ኢይትዌለጥ ፡ ወኢይትመየጥ ፡ እምህላዌሁ ፡ እስመ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወቦቱ ፡ አካል ፡ ፍጹም ፡ ከመ ፡ አቡሁ ፡ ወኢፈጠረ ፡ ሎቱ ፡ ሥጋ ፡ ዘኮነ ፡ ፩ደ ምስሌሁ ፡ እምህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ አላ ፡ ነሥአ ፡ እምኔነ ፡ እሙነ ፡ ወኢኮነ ፡ ልደቱ ፡ እምዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ በአስተሐውዞ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ አላ ዳእሙ ፡ ተወልደ ፡ እምድንግል ፡ ቅድስት ፡ በመንክር ፡ ግብር ፡ ዘኢይትነገር ፡ ወይትሌዐል ፡ እምልቡና ፡ ወፍሉጥ ፡ እምሕገ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

፲፯ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እንዘ ፡ ያወሥእ ፡ ለአቡሊናርዮስ ረሲዕ ፡ ረስዮ ፡ ለሥጋ ፡ ይልህቅ ፡ በበሕቅ ፡ በከመ ሥርዓተ ፡ሰብእ ፡ በዘይደሉ ፡ ለሥጋ ፡ ከመ ፡ ኢይረስይዎ ፡ ለዐማኑኤል ፡ አምላክነ ፡ ውፁአ ፡ እምልማደ ፡ ሰብእ ፡ በካልእ ፡ ምግባር ፡ ወተመሰለነ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአሁ ፡ ኢርሒቀ ፡ መለኮት፡ ወኢተፈልጠ ፡ እምእሉ ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ በከመ ፡ ሥርዓት ፡ እንተ ፡ ዘሥጋዌ ፡ መፍቅድ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ተሠግዎቱ ፡ ለመድኀን ፡ ከመ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ።

## ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፬ ።

### ክ ፍ ል ፡ ፡ ፪ ።

፲፬ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ እንደሆነ ፤ በብቻው ፡ ያለ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ እንዳይደለ ፡ ሲያስረዳ ፤ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ወደ ፡ ነገሥት ፡ (አርቃደዮስና ፡ ቴዎዶስዮስ) ከላከው ፡ መልእክት፤ ደቀ፡ መዝሙሩ ፡ ጴጥሮስ በሃይማኖት ፡ በማስተዋል ፡ ክርስቶስ ፡ በፈቃዱ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡እንዳልታመመ ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ ተናገረ ፡ እሱ ፡ ከሕማም፡ሁሉ የራቀ ፡ ነው ፤ ሕማምም ፡ ከእሱ ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ ዛሬ ፡ ግን ፤ በሥጋ ፡ ብቻ ፡ ታመመ ፤ ሰው ፡ እንደ መኾኑ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፤ አምላክ ፡ እንደ ፡ መሆኑ በባሕርዩ ፡ ሕማም ፡ የሌለበት ፡ ነው ፤ ተብሎ ፡ ስለ እሱ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፤ ሰው ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ በተዋሕዶ ፡ እንደ ፡ ከበረ ፡ እናውቀዋለን ፤ ግን ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ራሱን ፡ የሚያከብር ፡ እሱ ፡ ነው ።

፲፭ ፡ አንድነትን ፤ ሦስትነትን ፡ የተናገረ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ወደ አቅላንድዮስ ፡ በላከው ፡ መልእክቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ የሚታመም ፤ በመለኮቱ ፡ የማይታመም ፤ እሱ ፡ በሥጋ ፡ ይወሰናል ፤ በመለኮት፡ አይወሰንም ፤ እሱስ ፡ መቾም ፡ መች ፡ ሰማያዊ ፡ ነው ፤ ምድራዊም ፡ ነው ፤ ይታያል ፤ አይታይም ፤ ይመረመራል ፤ አይመረመርም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሲኾን ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ በኃጢአት ፡ ወድቆ ፡ የነበረ ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ እንደገና ፡ አደሰ ።

፲፮ ፡ ዳግመኛም ፤ የሃይማኖት ፡ ዐምድ ፡ መምህር ፡ ሊቀ ጳጳሳት ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ከሐዲው ፡ አቡሊናርዮስን ፡ ሲከራከረው ፡ በተናገረው ፡ ድርሳኑ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃልስ ፡ ሕማም ፤ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ነው ፤ ከባሕርዩም ፡ አይለወጥም ፤ አይፋለስም ፤ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ እንደ፡ አባቱ ፡ ያለ ፡ ፍጹም ፡ አካል ፡ አለው ፤ ከእሱ ፡ ጋር አንድ ፡ የኾነ ፡ ሥጋንም ፡ ሊዋሐደው ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ አልፈጠረም ፤ በውነት ፡ ከእኛ ፡ ባሕርይ ነሣ ፡ እንጂ ፤ ከሰው ፡ ወገን ፡ መወለዱም ፡ ሰው ፡ ደስ ብሎት ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ አይደለም ፤ በማይመረመር ፤ ከልቡና ፡ በራቀ ፡ ከሰው ፡ ባሕርይ ፡ ልማድ ፡ ልዩ ፤ ድንቅ ፡ በኾነ ፡ ሥራ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ተወለደ ፡ እንጂ ።

፲፯ ፡ ዳግመኛም ፡ ከሐዲው ፤ አቡሊናርዮስን ፡ ሲከራከረው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ የሰው ፡ ሥርዓት ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ በሥጋ ፡ በሚገባ ፡ መጠን ፡ ሥጋን ፡ በየጥቂቱ እንዲያድግ ፡ አደረገው ፡ ፈጣሪያችን ፡ ዐማኑኤልን ምትሃት ፤ ኅድረት ፡ በማለት ፡ ከሰውነት ፡ ሥርዓት ፡ የወጣ ፡ እንዳያደርጉት ፤ ከኃጢአት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ መሰለን ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ዳግመኛ ፡ የተወደደ ፡ የሥጋዌ ፡ ሥርዓት ፡ እንደ ፡ መኾኑ መለኮት ፡ ከእነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ ባሕርያት ፡ ከነፍሱ ፤ ከሥጋው ፡ አልተለየም ፤ አልራቀም ፡ ብሎ ስለ ፡ እርሱ ፡ ተናገረ ፤ ዳግመኛም ፤ መድኀን ፡ ሰው፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ሲናገር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተናገረ ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፱ ።

፴፭፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ በመጽሐፈ ፡ መዝገብ ፡ ቃለ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ወዘፈጠረ ፡ ሥጋ ፡ ፈጠረ፡
ሰብአ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እግዚእ ፡ ለኵሉ ፡ አሐዱ ፡
ቀዳሚ ፡ ለፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወተግባሩ ፡
እስመ ፡ ቀዳሚሁሰ ፡ እሳት ፡ ውእቱ ፡ ወሕይወት፡
ክርስቶስ ፡ ዘኢይጻወር ፡ ወእምድኅረ ፡ ኀዳጥ ፡
ይቤ ፡ እመሰ ፡ ሰብአ ፡ ኮነ ፡ ወይፈጽም ፡ ግብረ ፡
ይኩን፡ ፍኖተ ፡ ቀዳማየ ፡ ወከመዝ ፡ እሙነ ፡ ንብል
በእንቲአሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር፡
ፈጠረኒ ፡ ቀዳሚ ፡ ለፍኖተ ፡ ሠናይቱ ፡ ውእቱሰ ፡
ኢፈጠረ ፡ ከመ ፡ ይባእ ፡ ውስቴቱ ፡ አላ ፡ ውእቱሰ፡
ቀዳማዊ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወህልው ፡ ዘልፈ ፡ ፈጠረ፡
ሥጋሁ ፡ በእንተ ፡ ምክንያት ፡ ዘተነግረ ።

፴፮፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እመሰ ፡ ኮንከሙ ፡ ተአምኑ ፡ ከመ
ክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ ሰብአ ፡ እሙነ ፡ ወእሮኑ ፡ ኢይደ
ልወነ ፡ ከመ ፡ ንብል ፡ ዘይደሉ ፡ ለሰብእ ፡ ዘእን
በለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፤ ወይደሉ ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡
ንበል ፡ አንሰ ፡ ኢሀሎኩ ፡ ቀዳሚ ፡ ሰብአ ፡ ዝኩ ፡
ዘይደሉ ፡ ለህላዌ ፡ መለኮት ፡ ባሕቲቱ ፡ ወንዕቀብ ፡
ዓዲ ፡ ዘይደሉ ፡ ለህላዌ ፡ ዘበአማን ፡ ዘተፈጥረ ፡
እስመ ፡ ሰብእሰ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ፡ ወበእንተ ፡
ዝንቱ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኒ ፡
በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ።

፴፯፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እመጽሐፍ ፡ እንተ ፡ ዘቅዱስ ፡ ቄር
ሎስ ፡ በውስተ ፡ ቢሶርስ ፡ በከመ ፡ ኀይል ፡ ለሊሁ ፡
ኀይል ፡ ውእቱ ፡ ኵለንታሁ ፡ ወኢይደክም ፡ ኢይ
ትበሀል ፡ በእንቲአሁ ፡ ርኅበ ፡ እስመ ፡ ለሊሁ ፡
መብልዕ ፡ ወሕይወተ ፡ ኵሉ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡
ረሰየ ፡ ሥጋሁ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ዝንቱ ፡ ዘፍ
ጥረቱ ፡ ይርኅብ ፡ ወይጸምዕ ፡ ወይደክም ፡ ወከመዝ፡
ኮነ፡ ይጔልቍዎ ፡ ምስለ ፡ ኃጥአን ፡ ዝንቱ ፡ ዘጾረ ፡
ኃጢአተነ ፡ ወተፀገሠ ፡ ሕማመነ ፡ በፈቃዱ ፡ ወሞተ
ቤዛነ ፡ ተሰቅለ ፡ ክርስቶስ ፡ አኮ ፡ ከዊኖ ፡ ርጉመ ፡
ዳእሙ ፡ ከመ ፡ ያሰስል ፡ መርገመ ፡ ዘቦአ ፡ ውስቴታ
አቡነ ፡ አዳም ፡ ተፀገሠ ፡ ለተሰቅሎ ፡ በእንቲ
አነ ፡ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ዘተዋሐደ ፡ ወኮነ ፡
ሰብአ ፡ ወተፀገሠ ፡ ለተወልዶ ፡ ከማነ ፡ እምኢይቤ
ዘንተ ፡ ይቤ ፡ አላ ፡ ዘንተ ፡ በእንተ ፡ ዘውእቱ ፡ እም
ድንግል ፡ ቅድስት ፡ በአምሳል ፡ ዘይደሉ ፡ ለትስ
ብእት ።

ስምዓት ፡ ም ፡ ፻፳፱ ።

፴፭፤ ዳግመኛም ፤ መዝገብ ፡ በሚባል ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ
አለ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፤ የፈጠረ፡
ለሁሉ ፡ ገዢ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሰውን ፡ ፈጠረ ፤ እግ
ዚአብሔር ፡ ላሰበው ፤ ለፈጸመው ፡ ሥራ ፡ ጀማሪው
አንድ ፡ ነው ፤ ክርስቶስ ፡ ጥንቱን ፡ የማይዳሰስ ፡
እሳት ፤ ሕይወትም ፡ ነው ፤ ጥቂትም ፡ እልፍ ፡ ብሎ
ሰው ፡ ቢኾንና ፡ መሪ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሥራን ፡
ቢሠራ ፡ ለቸርነቱ ፡ ሥራ ፡ ጀማሪ ፡ አድርጎ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ፈጠረኝ ፡ አለ ፡ ብለን ፡ እንዲህ ፡ ስለ ፡ እሱ
ብቻ ፡ በእውነት ፡ እንናገራለን ፤ እሱስ ፡ ሊያድር
በት ፡ አልፈጠረውም፤ በጊዜው ፡ ሁሉ ፡ በቅድምና፡
የነበረ ፤ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ተነ
ገረው ፡ ምክንያት ፡ ሥጋን ፡ ፈጠረ ፡ እንጂ ።

፴፮፤ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ እን
ደኾነ ፡ በውነት ፡ ካመናችሁ ፡ ከኃጢአት ፡ ብቻ
በቀር ፡ ለሰው ፡ የሚገባውን ፡ ልንናገር ፡ እንደምን ፡
አይገባንም ? ዳግመኛም ፡ እኔ ፡ ቀድሞ ፡ ሰው ፡ አል
ነበርኩም ፡ አለ ፡ ልንል ፡ ይገባናል ፤ ይህ ፡ የሚገባው
ለባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ዳግመኛም ፤ በው
ነት ፡ ለተፈጠረ ለሥጋ ፡ ልንጠብቅ ፡ ይገባናል ፡
ሰው ፡ ፍጡር ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፤ ሰው ፡ ስለኾነ ፡
እግዚአብሔር ፡ ፈጠረኝ ፡ ይላል ፡ አለ ።

፴፯፤ ዳግመኛም ፤ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ በጻፈው ፤ ቢሶርስ ፡
በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እሱ ፡ ኀይል
እንደ ፡ መኾኑ ፡ ሁለንተናው ፡ ኀይል ፡ ነው ፤ ድካም
የለበትም ፤ እሱ ፡ ተራበ ፡ አይባልም ፤ እሱ ፡ የሁሉ ፡
ሕይወት ፤ የሁሉ ፡ ምግብ ፡ ነውና ፤ በተለየ ፡ አካሉም
ሥጋን ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ ባሕርዩ ፡ የሚራብ ፡ የሚ
ጠማ ፤ የሚደክም ፡ ይህ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ ከኃ
ጥአን ፡ ጋር ፡ ይቈጥሩት ፡ ነበር ፤ ኃጢአታችንን ፡
የተሸከመ ፤ በፈቃዱ ፡ የእኛን ፡ መከራ ፡ የተቀበለ፤
ስለ ፡ እኛ ፡ ቤዛ ፡ ኾኖ ፡ የሞተ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ ክርስ
ቶስ ፡ ተሰቀለ ፤ ግን ፡ መርገም ፡ ኖሮበት ፡ አይደለም፤
አባታችን ፡ አዳም ፡ ተይዞበት ፡ የነበረ ፡ መርገምን፡
ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ስለ ፡ እኛ ፡ መሰቀልን፤
ወደደ ፤ የተዋሐደ ፤ ሰው ፡ የኾነ ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ መወ
ለድን ፡ የወደደ ፤ ሥጋ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ባላ
ለም ፡ ነበር ፤ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ሥጋ
ለትስብእት ፡ በሚገባው ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ እንጂ።

